ETHIOPIAN UNITY PATRIOTS FRONT

# የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር

ኢ.አአግ EUPF

አንድ ሀገር
አንድ ሕዝብ
አንድ ሰንደቅ ዓላማና
አንድ የጋራ ዕድል

ONE COUNTRY
ONE PEOPLE
ONE FLAG & ONE
COMMON DESTINY

ልዩ እትም　　　　ግንቦት 1998 ዓ.ም.

## ከኢትዮጵያዊነት የራቀ ልብና ከሕዝባችን ጥቅም ፍላጐት ውጭ የሚፈጠር ሕብረት የእንቧይ ካብ ነው::

ሀገራችን ለምትገኝበት የተወሳሰበ ችግርና ለሕዝባችን ጉስቁልና በቅድሚያ በሐላፊነት የሚጠየቀው ወያኔ ነው:: መጠየቅም ብቻ ሣይሆን ለታሪክ ፍርድ የሚቀረብ ነው::

ወያኔው ከመነሻውም ይሁን ከአመጣጡ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ለማጥፋት አጀንዳ ያለው በመሆኑ በአለፉት 15 ዓመታት የሥልጣን ዘመኑ ድብቅ ዓላማውን እውን ለማድረግ በስፋት ተንቀሳቅሷል :: በአሁኑ ወቅትም የቀረ ተልእኮውን ለማሟላት በፍፁም አምባገነናዊነት ስሜት ሀገርና ሕዝብን እየገደለ ይገኛል::

በአንፃሩ ደግሞ ይህን የወያኔ የጥፋት ተልእኮ ለመከላከልም ሆነ ከስሩ ለመበጠስ ያስችል ዘንድ ቁጥራቸው ቀላል ያልሆኑ ተዋቃሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ተመስርተዋል:: ከማይጨበጥ ተስፋ በስተቀር ግን ያስገኙት አንዳችም ፋይዳ የለም ምክንያቱም ከሀገርና ከሕዝብ ፍላጐትና ጥቅም ይልቅ ሁሉም የየራሱ ኘሮግራም ጥገኛ ለመሆን የሚያደርገው ስግብግብነት ዋናው ማነቆ ነው ብለን እናምናለን::

ብዙ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች የመኖራቸውን ያህል ብዙ ሕብረቶችም ተመስረዋል:: አብዛኞቹ የእርስ በእርስ መደነቃቀፍ እየፈጠሩ ሕብረታቸው ከስም ዛሬ ከአንድ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከሌላው ጋር ለመሆን ሲባዝኑ ይታያል:: ምክንያቱም የፈጠራ የፖለቲካ አጀንዳና የማይዋልል መሠረታዊ አላማ ያለመኖር ጉድለት የፈጠረውና እየፈጠረ የሚገኘው አብይ ችግር ነው::

የሀገራችን የተቃዋሚ ኃይሎች አሰላለፍ ሁለት መልኮች አሉት ። አንደኛው ሀገራዊ አጀንዳ ይዞ የሚንቀሳቀስና ሌላኛው ደግሞ በተፃራሪነት ቆሞ ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያዊነት ማዶ በተገተረ እምነት የሚንቀሳቀስ ነው። በጥቅል ሲታይ በኢትዮጵያዊያንና በፀረ-ኢትዮጵያዊያን መካከል የሚደረግ ትግል ነው። ይህም አፍራሽ አላማ የወቅቱን ገዥዎች ፍላጐት ማእከል ያደረገ በመሆኑ ወያኔም በቀደምት ተዋናይነት በመሆን የፀረ-ኢትዮጵያውያን ዓላማ አስፈጻሚ አካል ነው።

በዚህ ምስቅልቅሉ በወጣ የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ ሀገራችን የገጠማትን ችግር ለማስወገድ በተለይም በአንድነቱ ጐራ የተሰለፈው ኃይል ለዓመታት ሣይሆን ለአፍታ ቆመን ጊዜን በመስጠት በሰከነ አእምሮ ማሰብ ይገባናል። የአባባሉን ትርጓሜ ወይም የሚያስገኘውን የጋራ ጥቅም ማንም ያጠዋል ብለን ባንገምትም አንድነት ኃይል ነው ልዩነት ፈንጅ ነው። ትልቁ ነገር አንድነት ለመፍጠር ምን ያህል ዝግጁ ነን። ሁሉም ተቃዋሚ ኃይል በየመዛግብቱ ላይ ያስቀመጠውን የድርጊት ኘሮግራም ወደ አንድ የጋራ አመለካከት ( መርህ) ለመምጣት ቁርጠኝነት አለን ወይ? ፈታኝ ጉዳዮች ይመስሉናል። ቅን ልቦናና ሐሜት የማይበርዘው አስተሳሰብ ካለን ጉዳናው አቀበት የለውም። በተለይም ዛሬ ሀገራችን ከአለችበት ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ሲታይ ተቃዋሚው ኃይል የየራሱን የፖለቲካ አጀንዳ ከባድም ይሁን መለስተኛ ኘሮግራም ለሕዝብ አቅርቦ በሕዝብ ምርጫ የፖለቲካ ስልጣን ለመያዝ ውድድር የሚካሄድበት ጊዜ አይደለም። ይህን ለማድረግ በቅድሚያ ሀገርና ሕዝብ መዳን አለበት ወያኔው በሕዝባችን የስልጣን ባለቤትነት አያምንም። ሽንፈቱን አልተቀበለም። ለመቀበልም ፈቃደኛ አይደለም።

ይህን ዘረኛና-አምባገነናዊ ስርዓት ማስወገድና መለወጥ ከተቻለ ሁሉም እራሱን በሚመስለው አደራጅቶ መሪም ተመሪም ለመሆን ይበቃል። የሕዝባችን ጥያቄ ግልፅ ነው። ከእስር፤ ከሞት፣ ከስደት እንዳን ነው? ከአምባገነኑ የወያኔ አረመኔያዊ አገዛዝ ታደጉን ነው ለመብቱ መከበርና ለሕልውናው መረጋገጥ ብሎም ሞቶ አሣይቶናል። ተባባሩ ወይም ተሰባበሩም ብሎናል።

ትግሉ የሕይወት መስዋእትነት የግድ ይጠይቃል ምን ያህል ዝግጅ ነን። ወይስ ንጋት ላይ የማይደርስ ሕብረት እየፈጠርን በተጋጋለ የሕዝብ ትግል ላይ የበረዶ ወሃ በመጨመር ማቀዝቀዝ ዓላማዬ ብለን ከያዝነው ሞቱ የጋራችን ነው።

ስለዚህ በጠራ የፖለቲካ አቋም ሕብረት ወይም ውሕደት መፈጠር የሁሉም ተቃዋሚ ኃይሎች መሪ አጀንዳ ሊሆን ይገባዋል ። በኦነግ ከተደራጀው ሕብረት ባሻገር ማለታችን

ነው:: እንደማታወቀው በሻአብያ ፊት አውራሪነትና በኦነግ አቀንቃኝነት ተፈጠረ የተባለውን የሕብረት ስምምነት አይደተናል:: ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጐትና ጥቅም በተፃራሪነት የተሰለፈው ሐይል ከቅንጅትና የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነት ግንባር ከሚሰኘው በስተቀር ሁሉም ለመንደር ፖለቲካ ስኬት የቆሙ ናቸው:: ሁለቱ ሃገራዊ ድርጅቶች በተለይም ቅንጅቱ ካለው ሕዝባዊ ድጋፍ ከሚከተሉው ግልፅም የፖለቲካ አቋም አንፃር በጠባብ ብሔርተኞች ስብስብ ውስጥ መዘፈቁ ግራ ያገባል በእርግጥ የመሪዎቹን ( የአስተባባሪዎቹ) ውሳኔ ለመጋፋት ውክልናው ባይኖረንም የሚከተለው የአሉታዊ ተፅእኖ ከወዲሁ ለማመልከት ብቻ ነው::

ኦነግ የወያኔው መሣሪያ በመሆን ያገለገለና በስልጣን ክፍፍል ላይ ቦታ በማጣቱ አኩርፎ ያፈነገጠ ነው:: ነገ ስልጣን ቢሰጠው ተመልሶ የሚያበጣብጥ ነው:: ዛሬም ደግሞ ቢጤዎቹን ሰብስቦ የተቃዋሚዎች ሕብረት ፈጥሬአለሁ ይለናል:: በእርግጥ ሻኣብያ ወያኔን በመፍጠር ኢትዮጵያን እንዳዳከመ ሁሉ ዛሬ ደግሞ ኦነግንና መሰል ጠባቦችን አሰባስቦ ጭራሽ ኢትዮጵያን መናሯን ለማጥፋት ያደራጀው ሐይል ለመሆኑ የሚያነጋግር ወይም የሚያፈላስፍ አይመስለንም:: በእርግጥ ይህ የኦነግና የጐጠኞች ሕብረት ለወያኔና ሻአብያ ድል ነው ምክንያቱም ከስልጣን ልዩነት በስተቀር የአላማ ልዩነት የላቸውም::

አንድ ነገር ማሰብ ይቻላል ከተቻለም በርቀት በእርግጥ ኦነግና ቢጢዎቹ በእስከ አሁኑ ሒደት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጐትና ጥቅም በተፃሪሪነት መቆማቸውን አውቀው ይሆን ?

ለጋራ ሃገራችን ለጋራ ጥቅማችን እኛ ለጋራ እድላችን ስኬት በጋራ ለመንቀሣቀስ አስበው ከሆነ እሰው፤ ለዚህ ደግሞ ከልብ የመነጨ ማረጋገጫ ያስፈልጋል:: ስሕተትን አምኖ መቀበል :: መወቃቀስ ፣ መተማመን መደጋገፍ በተቀጣይትም ለሐገራችንና ለሕዝባችን እድገት መታገል :: ይህ በሌለበት ሁኔታ ግን ከኢትዮጵያዊነት የራቀ ልብና ከሕዝባችን ፍላጐት ውጭ የሚመጣም ሆነ የሚፈጠር ሕብረት የአንባይ ካብ ነው:: ተግባራችን ሁሉ የማንታችን መግለጫ ስለሆነ የምንሰራው ለማደግና ለመታየት ሣይሆን ለንፁሕ ሕሊና ይሁን:: ከታሪክ ፍርድ ለማምለጥም ይሁን ለመዳን እኛነታችንን ለሕዝባችን በሐቀኝነት እናስገዛ::

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

ሰልፍ የጀግና ድል የእግዚአብሔር ነው::